# ለቀድሞ የኢሕአፓ አባላት
## ከአሲምባ የውይይት መድረክ

ክቡራትና ክቡራን የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት (ጓዶቻችን)

ከሁሉ አስቀድመን በዚህ ሁለት ቀናት ለሚደረገው የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት ስብሰባ ሙሉ ድጋፋችንን እየገለጽን፤ ውይይታችሁ የተሳካና ፍሬአማ እንዲሆን እንመኛለን። ለዚህም ድጋፋችን መሠረቱ ይህ ስብሰባና የአሲምባ የውይይት መድረክና እህት ድረ-ገጹ (አሲምባ ዳት ኦአርጂ) የምሥረታ ዓላማዎች አብረው መሄድ መቻላቸውን ስለምናምንበት ነው።

ክቡራትና ክቡራን፤

የአሲምባ ውይይት መድረክና ድረ-ገጹ የተመሠረቱበት ወቅት የወያኔ መንግሥት በዘጠና ሰባቱ ምርጫ ማግስት ያታልልበት የነበረውን የዲሞክራሲ ሽርጥ አውልቆ ጥሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድሮውንም ግልጽ የነበረውን ፋሻሽታዊ ገጽታውን ይዞ በዓለም መድረክ ላይ ብቅ ያለበት የቀውጢ ጊዜ ነበር። ይህም ሁኔታ አዲሱ ትውልድ ለሚጠብቀው መራራ ትግል፤ ሊመረምረውና ሊማርበት የሚገባ፤ በዛሬዩቱ ኢትዮጲያችን የተንሠራፋው የዘረኞች፤ የጎጠኞችና፤ የሆዳሞች መንጋ የሚከላለሰውን፤ በጀግንነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባላቸው ፍቅር፤ ለፍትኅና ለዲሞክራሲ፤ በውድ ሕይወታቸው ምስወዕትነት ያዳበሩትን የዚያን ትውልድ ጅግኖች የትግል ታሪክ፤ ሳይቀነስ፤ ሳይበረዝና ሳይደለዝ፤ አሁንም በሕይወታቸው ከሚኖሩ የትግል ጓዶቻቸው፤ የሥራ ባልደረቦቻቸው፤ ወዳጆቻቸውና ቤተ-ዘመዶቻቸው ተሰባስቦ፤ ዕውነቱ በትክክል እንዲቀርብ ከመቼውም የበለጠ አንገብጋቢ አድርጎታል።

ከዚህም ሌላ ይህ መድረክ ባለፉት አርባ ዓመታት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትኃዊ ነፃነት ሲታገሉ ለወደቁ፤ በደርግ ፋሺሽታዊ ሥርዓት በቀይ ሽብር ሠለባ ለሆኑ፤ ለሕዝባችን ነፃነት እንታገላለን በሚሉ ጠባብ ብሔረትኞች ለተጨፈጨፉ፤ በፅናታቸው፤ በኢትዮጵያዊነታቸው ተግዘው ለማቀቁና አሁንም በየጉድባው አሣራቸውን ለሚቀጥሩ፤ ከምድረ-ገጽ ደብዛቸው ለጠፋ የቁርጥዩ ቀን የኢትዮጵያ ጀግኖችና በዓለም ዙሪያ ካለውዴታቸው ተሰደው ለሚኖሩ ታጋዮች መተሰቢያ እንዲሆን ታስቦ ነው።

ኢትዮጵያ በምትባል ሀገራችን ክልል ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ በማንም ቅኝ ሳይገዛና ሰይወረድ ለዘመናት የኖረው እንዲያው በታሪክ አጋጣሚ አይደለም። የዛሬዎቹ ዘረኞች እንደሚያንበለብሉትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪከ የመቶ ዓመት ብቻም አይደለም። ይልቁንም ታሪካችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጋራ ነፃነት በተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች ላይ በአንድነት ድንበር ጥሰው ከመጡ ጠላቶቹ ጋር በመዋደቅ በደሙ ጽፎ ያለፈው እንጂ። ለዚህም ብዙ ሳንርቅ አያቶቻችን እንደ አድዋና የአምስቱ ዓመታት ፀረ-ጣልያን የነፃነት ወይም ሞት የጋራ ትግል የከፈሉትን መሥዋዕትነት መመልከት በቂ ነው። በኛም ዕድሜ ቢሆን ያ ትውልድ ለጋራ ፍትኃዊ ሥርዓት መመሥረትና ለዲሚክራሲ፤ በዘር ሳይከፋፈል ያደረገው መዋደቅ ለሁሉም ኢትዮጲያዊ መሆኑ የማይካድ ኃቅ ነው። ይህንን አሌ የሚሉ ካሉ የዛሬዎቹ የጥፋት መደካኪያዎች፤ ዘረኞችና ለሆዳቸው ያደሩ ባንዳዎች ብቻ ናቸው። አዲሱን ትውልድ የውሸት ታሪክ የሚግቱትም ቆራጥነትን፤ መሥዋዕትነትንና ጀግንነትን ሊሠልቡት፤ በዘረኝነትና በግለኝነት የሚመጣን ባርነት አሜን ብሎ ተቀብሎ፤ ተሸቆጥቁጦ እንዲገዛ ለማመቻቸት ብቻ ነው። ስለሆነም ይህ መድረክ ሲመሠረት የዚያ ትውልድ ተምክሮ በቀጣይነት ለዛሬው ትውልድ ተላልፎ ከጠንካራው ጎኑ እራሱን እንዲያንፅበት፤ ደካማውን እንዳይደግም የምንማማርበት እንዲሆን ታስቦ ነው።

ክቡራትና ክቡራን፤

በኛ እምነት ጓዶቻችን መሥዋዕትነት የከፈሉበት የዲሞክራሲ፤ የፍትህና የዕኩልነት ጥያቄ ዛሬም ሕዝባችን የሚዋደቅበት ነው። ሰለሆነም እያንዳንዳችን በዚህ የሞት የሽረት ትንቅንቅ ወቅት ሊኖረን የሚገባውን ሚና ልንመረምር የሚገባን ጊዜ አሁን ነው ብለን እናምናለን። ስለሆነም፤ በመድረካችን በዚህ ጉዳይ ላይና ስለዚህ ስብሰባ በሰፊው ከተወያየን ባኋላ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ የስብሰባው ተካፋዮች አበክረው እንዲያጤኑት እናሳስባለን።

1. በመካከላችን የነበሩትን መሠረታዊ ልዩነቶች በሚገባ ተወያይተን በመፍታት ኢሕአፓን ተቀላቀሉ እንቀላቀል እንላለን።

2. ወደ ድርጅቱ በተለያዩ ምክንቶች መቀላቀል እንችልም ለምንል ደግሞ ለኢሕአፓ የአቅማችንን የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፍ እናድርግ እንላለን።

3. ወደ ድርጅቱም አንቀላቀልም፤ ዕርዳታም አናደርግም የምንል ደግሞ ኢሕአፓ የዚያ ትውልድ ፈርጦች፤ በሕይወታቸው ሕይወት የሰጡን ጀግኖች ቤት መሆኑን ሳንዘነጋ መሠረት በሌለው ጥላቻ ከምናደርገው ጥቃት እንቆጠብ እንላለን።

የአሲምባ የውይይት መድረከ

ድል ለኢትዮጲያ ሕዝብ!
ኢትዮጲያዊነት ያለጥርጥር ያቸንፋል!